# 🍒 ዝክረ ቃል [መጽሐፈ ዚቅ] በግእዝና በአማርኛ ማስታዎሻ 🍒



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፰፣ ፳፻፲፭ ዓ.ም

## 🍒 ዝክረ ቃል [መጽሐፈ ዚቅ] 🍒

ዚቅ መልክአ በቅደም ተከተል ከተጻነጸለ በኋላ ከመልክኡ ዝቅ ብሎ የሚደርስ በመሆኑ ዚቅ ተብሏል:: በአንድ ዘመን የተደረሰ ሳይሆን በየጊዜው እየተከናወነ የመጣ ነው:: በምሥጢር የሚጸነጸለውን መልክአ ይመስላል::

### 🍍ዘዮሐንስ🍍

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም ሆይ ጌልጌል ከተባለ ሰማይ አዳራሽ ዓውደ ዓመቱን ለመባረክ ለምሕረት ነይ:: ድንግል ሆይ እኛን ትባርኪን ዘንድ ከወዳጅሽ ልጅሽ ከዮሐንስ ጋር ነይ:: (#በግእዝ፦ ዐውደ ዓመት ለባርኮ እምጽርሐ አርያም ጌልጌል:: ማርያም ንዒ ለምሕረት ወሣህል:: ንዒ ኀቤየ ኦ ድንግል ምስለ ወልድኪ ፍቁርኪ ዮሐንስ ከመ ትባርኪ ላዕሌነ)::

**ነገረ ክርስቶስ፦** የመካን [የኤልሳቤጥ] ልጅ ለድንግል [ለማርያም] ልጅ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ አውቆ ከሴት የተወለደውን በጨለማ ውስጥ [ላሉ የመጣ] ብርሃን አለው:: የእግዚአብሔር ቃል ከድንግል ተወልዶ ታየ:: [አቤቱ] ወዳዘዝከን እንሰማራና እንገባ ዘንድ የጥበብን መብራት በልባችን ውስጥ አብራ:: (#በግእዝ፦ ሰመዮ ብርሃነ በውስተ ጽልመት ለዘተወልደ እምብእሲት አእሚሮ እምከርሠ እሙ ሰገደ ወልደ መካን ለወልደ ድንግል:: ቃለ እግዚአብሔር እምድንግል አስተርአየ:: ማኅቶተ ጥበብ ውስተ አልባቢነ አኅቱ ኀበ አዘዝከነ ኑፈር ወንዕቱ)::

### 🍎መስከረም 2*ዘምትረተ ርእሱ🍎

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም የነቢያት ትንቢታቸው የሐዋርያት ስብከታቸው የሰማዕታት እናታቸው የመላእክት እኅታቸው ናት:: የትጉሃን መላእክት እኅታቸው የደጋጎች ነቢያት ልጃቸው ናት:: የሐዋርያት እናታቸው የጻድቃንና የሰማዕታት እናታቸው ናት:: ቤዛዊተ ዓለም ማርያም ሆይ በሚጠፍጥ ስምሽ መታሰቢያ ሁላችን እንደሰት:: የሚያምር በሆነ በዮሐንስ ደምም ደስ ይበለን:: ብሩህ ደመና የጋረዳትን መልአክ በሰላም ተናገራት:: ዳግሚት ሰማይ የተባልሽ ድንግል ሆይ ልብሽ ደስ ይለዋል ክብርሽም ከፍ ከፍ ይላል:: (#በግእዝ፦ ዛቲ ይእቲ ትንቢቶሙ ለነቢያት ስብከቶሙ ለሐዋርያት እሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት:: ዛቲ ይእቲ እኅተ ትጉሃን መላእክት ወለተ ኄራን ነቢያት፣ እሞሙ ለሐዋርያት ሞገሶሙ ለጻድቃን ወሰማዕት:: ንትፌሣሕ ኵልነ በዝክረ ስምኪ ጥዑም ወበደመ ዮሐንስ መዐድም ቅድስት ማርያም ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም:: ደመና ብሩህ ዘከለላ መልአክ በሰላም ተናገራ:: ይትፌሣሕ ልብኪ ኦ ድንግል ወይትሌዐል ቀርንኪ በክብር ሰማይ ዳግሚት)::

### 🍏መስከረም 3🍏

**ነገረ ክርስቶስ፦** ስለወለደችህ ስለማርያም ብለህ ስላጠመቀህ ስለዮሐንስም ብለህ ስለቅዱሳኖችህ ሁሉ ብለህ ሁልጊዜ በመስቀልህ ኀይል ርዳን:: አቤቱ በፊትህ አታሳፍረን:: (#በግእዝ፦ በእንተ ማርያም ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ መጥምቅከ ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ ርድአነ ወትረ በኀይለ መስቀልከ ኢታስተኀፍረነ እግዚኦ በቅድሜከ)::

**ነገረ ማርያም፦** የአቤልን መሥዋዕት የወደደው በማሕፀንሽ ተፀነሰ:: ነውር የሌለብሽ አዲስ መርከብ ሆይ ጸሎታችንን ስሚ:: (#በግእዝ፦ በማሕፀንኪ ተፀውረ መሥዋዕተ አቤል ዘሠምረ ጸሎተነ ስምዒ ወትረ ሐመር ሐዳስ ዘአልብኪ ነውረ)::

**❖መስከረም 5❖**

**ነገረ ክርስቶስ፦** በአብ ዘንድ ልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ መንፈስ፣ በድንግል ማርያም ዘንድ ሕፃን፣ በነቢያት ዘንድ ነቢይ፣ በሐዋርያት ዘንድ ሐዋርያ፣ በሰማዕታት ዘንድ አክሊል የሆነ መምህርና የማኅበር አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: (#በግእዝ፦ ዘበኀበ አብ ወልድ ዘበመንፈስ መንፈስ ዘበድንግል ሕፃን ዘበነቢያት ነቢይ ዘበሐዋርያት ሐዋርያ ዘበሰማዕታት አክሊል መምህር ሊቀ ማኅበር ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ)::

**ቤተክርስቲያን፦** በየጠዋቱ ከአራቱ ወንዞች የተገኘ ምልክትን የምትጠጣ ቤተክርስቲያንን የወንጌል ፈሳሾች ይከቧታል:: ከማቴዎስ መወለዱን ከማርቆስ ተአምራቱን ከሉቃስ ላም መባልን ከዮሐንስ በግ መባልን፤ ይህንን ሰምታ በዓልን በደስታ ታከብራለች:: (#በግእዝ፦ ወኃይዝተ ወንጌል የዐውዳ ለቤተክርስቲያን እምአርባዕቱ አፍላጋት እንተ ትሰቀይ ትእምርተ ለለጽባሑ እማቴዎስ ልደቶ ወእማርቆስ መንክራቶ እምሉቃስ ዜናዊ ተሰምዮ ላሕም ወእም ዮሐንስ በግዐ ወዘንተ ሰሚዐ ትገብር በዓለ በፍግዐ)::

**❤መስከረም 7❤**

**ቅዱስ ሚካኤል፦** ከቅድስት ቦታህ ሆነህ ሥላሴን የምታመሰግን ሚካኤል ሆይ የሚቃረነንን ሰይጣን አጥፋልን:: (#በግእዝ፦ እምቅድስት አፀድከ እንተ ትቄድስ ሥላሴ:: አሰስል ሚካኤል ዘይትቃረን ከይሴ)::

**ነገረ ማርያም፦** የቃል ማደሪያ፣ የጨረቃ ክበቡ፣ የፀሐይ ሙቀቱ የሆንሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ:: የአንቺን ፍሬ የበሉ ብልኻተኛ ይሆናሉ:: አንቺ ልብ የምታስደርጊ ዕፅ ነሽ:: እናታችንና የጌታችን እናት ማርያም ሆይ የምድር ነገሥታት ሁሉ ተሰብስበው ይሰግዱልሻል:: የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ:: (#በግእዝ፦ ተፈሥሒ ድንግል እግዝእትየ ለቃል መዝገቡ ለወርኀ ክበቡ ለፀሐይ ላሕቡ ፍሬ ዚኣኪ እለ በልዑ ይጠቡ አንቲ ዕፅ ዘያሌቡ:: ኵሎሙ ነገሥተ ምድር ተጋቢያሙ ይሰግዱ ለኪ ወይልሕሱ ጸበለ እግርኪ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ)::

**❤መስከረም 11❤**

**ሰማዕት፦** ሀገር በሰማዕታት ትዕግሥት ትድናለች:: ቦታም በጻድቅ ጸሎት ትከብራለች:: (#በግእዝ፦ በትዕግሥቶሙ ለሰማዕት ትድኅን ሀገር ወበጸሎተ ጻድቅ ትትፌሣሕ መካን)::

**መስከረም 12**

**ሥላሴ፦** ልዩ ጽኑዕ የሆነ አብ በአካል አንድ ነው:: ልዩ ጽኑዕ የሆነ ወልድ በአካል አንድ ነው:: ልዩ ጽኑዕ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ በአካል አንድ ነው:: የእግዚአብሔር መንፈስ በሚካኤል

በገብርኤልና በሌሎችም መላእክት አደረ:: (#በግእዝ፦ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ:: እስመ መንፈሰ እግዚአብሔር ተሰውጠ ላዕለ ሚካኤል ወገብርኤል ወላዕለ ኵሎሙ መላእክት)::

**ሚካኤል፦** ሚካኤል ጌታችን ነውኮ:: (#በግእዝ፦ እስመ ሚካኤል እግዚእነ)::

**ነገረ ማርያም፦** አንቺ የጥበብ ዕፅ ነሽ:: (#በግእዝ፦ አንቲ ውእቱ ዕፀ ጥበብ)::

## ❤መስከረም 17 ዘመስቀል❤

**መስቀል፦** የዕረፍት እንጨት፣ የባሕር ጸጥታ የሆነ የክርስቶስ መስቀል ዛሬ በቅዱስ ቦታው ተገኘ:: ዳዊት የአብ ቃል በእርሱ ላይ ስለተሰቀለበት ስለእንጨት መስቀል በትንቢት መንፈስ በአንተ ጠላቶቻችንን ሁሉ እንወጋቸዋለን አለ:: ዳግመኛም ከቀስት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠኻቸው አለ:: (#በግእዝ፦ ዕፀ አንህዮ ለባሕር ዛህኑ መስቀለ አልፋ ተረክበ ዮም በቅዱስ መካኑ:: ብከ ንወግዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ ይቤ ዳዊት በመንፈሰ ትንቢት በእንተ ዕፀ መስቀል ዘተሰቅለ ዲቤሁ ቃለ አብ:: ወካዕበ ይቤ ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምስጡ እምገጸ ቅስት)::

## ❤መስከረም 19 ዘገብርኤል❤

**ገብርኤል፦** ገብርኤል ሆይ በወርቅ መስቀልህ ትባርከን ዘንድ በእውነት በመካከላችን ተጫወት:: (#በግእዝ፦ ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ ገብርኤል ማዕከሌነ ተዋነይ በጽድቅ)::

## ❤መስከረም 21 ዘማርያም❤

**መስቀል፦** መስቀል ያረጀውን ዓለም አሳመረ:: በማርያም ውበት አበራ:: ለቤተክርስቲያን ታላቅ ሆነ:: (#በግእዝ፦ መስቀል አሠነየ ዓለመ እንተ በልየ በስነ ማርያም አዋከየ ለቤተክርስቲያን ኮኖሙ ዐቢየ)::

**ነገረ ማርያም፦** ጳውሎስ የነጻነት ድንኳን አላት:: ጴጥሮስም የብርሃን እናት አላት:: (#በግእዝ፦ ጴጥሮስኒ ሰመያ እመ ብርሃን ጳውሎስኒ ይቤላ ደብተራ ግዕዛን)::

**ነገረ ቅዱሳን፦** ሳይኖረን ሁሉ አለን:: የሚያውቀን ሳይኖር ብዙዎች ያውቁናል:: በሰማይ ባለ ቤታችን ለእኛ የተዘጋጀልንን ልብስ እንልበስ:: (#በግእዝ፦ እንዘ አልብነ ኵሉ ብነ እንዘ አልቦ ዘየአምረነ ብዙኃን የአምሩነ:: ንልበስ ልብሰነ ዘድልው ለነ በኀቤሁ ማኅደርነ ዘበሰማያት)::

## ❤መስከረም 23 ዘጊዮርጊስ❤

**ነገረ ማርያም፦** [ማርያም] የመመኪያችን ዘውድ፣ የዳዊት መሰንቆ የሰሎሞን ዘውድ ናት:: (#በግእዝ፦ አክሊለ ምክሕነ መሰንቆሁ ለዳዊት ወአክሊሉ ለሰሎሞን)::

## ❢ዘጽጌ ከመስከረም 26-ህዳር 6❢

**ነገረ ማርያም፦** በነቢያት አንደበት የተመሰገንሽ ነሽ፡፡ በሐዋርያትም የተመሰገንሽ ነሽ፡፡ የጊዮርጊስ የበረከት አክሊል የእስራኤል ወገን መመኪያ ነሽ፡፡ [ድንግል ማርያም] በቤተ መቅደስ የተተከለች ሎሚ እንዲሁም የጴጥሮስ ቁልፍ ናት፡፡ የድንግልን ተአምር ትሰሙ ዘንድ ቁማችሁ አድምጡ፡፡ የአብ ሙሽራ የበጉ እናት በሆነች በቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ፊት ጸልዩ፡፡ [ማርያም] የማትረግፍ አበባ ናት፡፡ እመቤቴ ሆይ የአብርሃም እርሻ የሙሴ እኅት የዳዊት ልጅ ነሽ፡፡ የከበረ ዕንቍ በውስጧ ያበራል፡፡ የልብሶቿ መዓዛ ሽቶዎች አሉት፡፡ በእሾህ መካከል ያበበች የሃይማኖት አበባ ናት፡፡ የቃሏ ጣዕም ከወይን ይልቅ ያምራል፡፡ (#በግእዝ፦ ውድስት አንቲ በአፈ ነቢያት ወስብሕት በሐዋርያት አክሊለ በረከቱ ለጊዮርጊስ ወትምክሕተ ቤቱ ለእስራኤል፡፡ ከርካዕ ዘተተክለት በቤተ መቅደስ መራኁቱ ለጴጥሮስ፡፡ ቁሙ ወአጽምዑ ተአምረ ድንግል ትስምዑ ጸልዩ ቅድመ ሥዕላ ለቅድስት ድንግል መርዓተ አብ ወእመ በግዑ፡፡ ጽጌ እንተ ኢትትነገፍ፡፡ እግዝእትየ ለአብርሃም ገራኅቱ ለሙሴ እኅቱ ለዳዊት ወለቱ ዕንቍ ክቡር ውስቴታ የሐቱ ጼና አልባሲሃ አፈዋት ቦቱ፡፡ በማዕከለ አሥዋክ ዘጸገየት ጽጌ ሃይማኖት፡፡ ወጣዕመ ቃላ ይሤኒ እምወይን)፡፡

**እግዚአብሔር፦** እግዚአብሔር ከቅድመ ዓለም እስከ ዘለዓለም በመንግሥቱ በመለኮቱና በሦስትነቱ አለ፡፡ ከቅዱሳን መካከል ምስጉን ሆኖ የተመሰገነ እንዳንተ ማን ነው?፡፡ አንተ የጻድቃን ምርኩዛቸው፣ ለተሰደዱት ተስፋቸው፣ ለሚታወኩት ወደባቸው ነህ፡፡ (#በግእዝ፦ እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም ሀሎ እግዚአብሔር በመንግሥቱ እግዚአብሔር በትሥልስቱ እግዚአብሔር በመለኮቱ፡፡ ስቡሐ ዘተሰብሐ በውስተ ቅዱሳን መኑ ከማከ፡፡ አንተ ውእቱ ምርጕዞሙ ለጻድቃን ተስፋሆሙ ለስዱዳን መርሶሆሙ ለእለ ይትሐወኩ፡፡

**አረጋዊ፦** ፍቅርን የተመላ አረጋዊ መዓዛው እንዳማረ ጽጌረዳ ነው፡፡ አረጋዊ የሕይወት ፍሬን የሚያፈራ የእውነት ወይን ቦታ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ አረጋዊ ምሉአ ፍቅር ከመ ጽጌ ረዳ ዘጥዑም ጼና መዓዛሁ፡፡ አረጋዊ አፀደ ወይን ዘጽድቅ ዘይፈሪ አስካለ ሕይወት)፡፡

**ትርጓሜ፦** በያዕቆብ እጅ የነበረው የኤሳው ጸጕር ወልደ እግዚአብሔርን ለሞት አሳልፈው የሰጡ የአይሁድ እጅ ምሳሌ ነው፡፡ (#በግእዝ፦ ጸጕርሰኬ ዘኤሳው ዘውስተ እዴሁ ለያዕቆብ እደ አይሁድ ውእቱ እለ አግብዕዎ ለሞት ለወልደ እግዚአብሔር)፡፡

## †ኅዳር 7 ዘጊዮርጊስ†

**ጊዮርጊስ፦** ጊዮርጊስ አምላኩን በመውደድ ተጋደለ፡፡ በርትቶ አክሊልን ተቀዳጀ፡፡ ሰማዕታት ወደ ሰማዕትነት ሲገቡ ሦስት ስሞችን ይይዛሉ፡፡ ክፉ ሐሳብንም ያሸንፉ ዘንድ ፊታቸውን በሥላሴ ያማትባሉ፡፡ መድኀኒታችን ለቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን በስምህ የሠራ ሁሉ በሰማይ ቤት እሠራለታለሁ አለው፡፡ ሰማዕታት በጠባብ ደጅ ገቡ፡፡ ሩጫቸውንም በሥላሴ ስም ፈጸሙ፡፡ የተመኙትንና የፈለጉትንም አገኙ፡፡ መንግሥተ ሰማያት ለእነርሱ ተሠራ፡፡ ለአንተ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ የተሰጠህ የሃይማኖት ዐለት ጊዮርጊስ ሆይ ወደ ክርስቶስ የሠርግ ቤት እንገባ ዘንድ ክፈትልን፡፡ (#በግእዝ፦ ጊዮርጊስ በፍቅረ አምላኩ ተጋደለ ገድለ ኀየለ ወተቀጸለ አክሊለ፡፡

ሶበ ይበውኡ ሰማዕት በውስተ ስምዕ ይፀውሩ ሠለስተ አስማተ ወየአትቡ ገጾሙ በሥላሴ ከመ ይማዕዎ ለእኩይ ጎሊና። ይቤሎ መድኀኒነ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ኵሉ ዘሐነፀ ቤተክርስቲያን በስምከ አነ አሐንጽ ሎቱ ማኅደረ ዘበሰማያት። ቦኡ ሰማዕት ጸባበ አንቀጸ በስመ ሥላሴ ፈጸሙ ምርዋጸ ዘተመነዩ ወኀሠሡ ረከቡ ገጸ መንግሥተ ሰማያት ሎሙ ተሐንፀ። ኦ ዘለከ ተውህበከ መራትት ዘመንግሥተ ሰማያት ኵኵሐ ሃይማኖት ጊዮርጊስ አርኅወነ ንባዕ ቤተ መርዓሁ ለክርስቶስ)።

**ቤተክርስቲያን፦** የነፍሳችን መድኀኒት የወንጌሉ ወንዞች ሆይ ሰላም ለእናንተ ይሁን። ቤተ መቅደሳችንን በጠዋት ኀብ፟ጿት። ይህቺ መቅደስ የሰማዕታትና የቅዱሳን ሁሉ እናታቸው ናት። (#በግእዝ፦ ሰላም ለክሙ ኦ አፍላገ ወንጌሉ ለመድኀኔ ነፍሳቲነ በጽባሕ ሐውጽዋ ለቤተ መቅደስነ። ዛቲ መቅደስ እሞሙ ለሰማዕት ወለኵሎሙ ቅዱሳን)።

**መስቀል፦** መስቀል ከዓለም ተስፋ ለሌላቸው ተስፋ ነው። (#በግእዝ፦ መስቀል ተስፋ ለእለ አልቦሙ ተስፋ እምዓለም)።

## 💟ሥላሴ💟

**ቅድስት ሥላሴ፦** ብርሃንን ለለየና ለረዳን ለእግዚአብሔር ምስጋናን እናቀርባለን። አምላካችንና መድኀኒታችን ይረዳናል። አምላካችንስ የማዳን አምላክ ነው። ለአብ ምስጋና ይገባል። ለወልድ ምስጋና ይገባል። ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል። (#በግእዝ፦ ሃሌ ሉያ ለእግዚአብሔር ለዘረድአነ ስብሐተ ንፌኑ ለዘፈለጠ ብርሃነ። ይረድአነ አምላክነ ወመድኀኒነ አምላክነሰ አምላከ አድኅኖ። ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ)።

## 💔ኅዳር 8 ዘ፬ቱ እንስሳ💔

**መላእክት፦** የማይተኙ ትጉሃን መላእክት በየሥርዐታቸው አንተን አብን ያመሰግናሉ። መላእክት ከሰማይ ወደ ምድር ሲወርዱ ድምፅ የላቸውም የክንፎቻቸው ድምፅም አይሰማም። ለእግራቸው ጫማ ዱካ የለውም። ሩጫቸው ከነፋሳት ይልቅ ይፈጥናል። (#በግእዝ፦ ትጉሃን እለ ኢይነውሙ መላእክት በበሥርዐቶሙ ኪያከ አበ ይሴብሑ። ሶበሰ ይወርዱ መላእክት እምሰማይ ዲበ ምድር አልቦሙ ድምፅ ወኢይሰማዕ ድምፀ ክነፊሆሙ አልቦ አሠር ለምክያዳተ እገሪሆሙ ይቀልል ሩጸቶሙ እምነፋሳት)።

**እግዚአብሔር፦** ቃልህ አይታበልም መንግሥትህም አይሻርም። ፊት አይቶ የማያዳላ በትክክል የሚፈርድ ነው። ከሠርክ እስከ ነግህ እንደጠበቅኾን ከነግህ እስከ ሠርክም ጠብቀን። (#በግእዝ፦ ኢይትሔሰው ቃልከ ወኢይሠዐር መንግሥትከ። ዘበርቱዕ ይኴንን ወኢያደሉ ለገጽ። ወበከመ ዐቀብከነ እምሠርክ እስከ ነግህ ዕቀበነ እግዚኦ እምነግህ እስከ ሠርክ)።

**ኪሩቤል፦** ይበራሉ ፊት ለፊት አይተያዩም። የመጀመሪያው ወዳመለከተበት ይሔዳሉ። በሠረገላ ይሮጣሉ። ምስጋናቸውም ድምፁ የሚያስፈራ ነው። (#በግእዝ፦ ይሠሩ ኢይትናጸሩ ኀበ አንጸረ ቀዳማዊ የሐውሩ በሠረገላ ይረውጹ ወስብሐቲሆሙ፡ኒ ዘመፍርህ ድምፁ)።

**ነገረ ማርያም፦** በወንጌል የተጻፈች በራሷ ላይ የመስቀል ምልክት ያለበት አክሊል ያላት የድንግል ክብሯና ትልቅነቷ ፍጹም ድንቅ ነው:: (#በግእዝ፦ መንክር ወመድምም ዕበያ ወክብራ ለድንግል ጽሑፍት ውስተ ወንጌል ወዲበ ርእሳኒ አክሊል በትእምርተ መስቀል)::

## 💖ኅዳር 9 ዘሠለስቱ ምእት💖

**እግዚአብሔር፦** ምስጋናው ከራሱ ዘንድ ነው ውዳሴውም ከራሱ ነው:: እርሱ ራሱ ዓለምን የያዘ ነው:: የበቀል ሰይፍ በእጁ አለ:: የግፉዓን ፍርድ ከአዳራሹ ይወጣል:: (#በግእዝ፦ ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ ወውዳሴሁ እምዚኣሁ አኃዜ ዓለም ለሊሁ ሰይፈ በቀል ውስተ እዴሁ ፍትሐ ግፉዓን ይወፅእ እምጽርሑ)::

**ጻድቃን፦** በብርድና በመራቆት በፍጹም ድካም ሰይጣንን አሸነፉት:: [አቤቱ] አንተ ነጻ የምታወጣ ኢየሩሳሌም ዋጋቸውን ሀገራቸው ጽዮንን ስጣቸው:: ክርስቶስ ሆይ በፍቅርህ መዓዛ ሰማዕታት መከራን ተቀበሉ:: ጻድቃንም በገዳማት ዞሩ:: (#በግእዝ፦ በቊር ወበዕርቃን በሐፍ ወበድካም ሞዕዎ ለሰይጣን:: አንተ ሀቦሙ አስቦሙ ጽዮንሀ ሀገሮሙ ኢየሩሳሌም አግዓዚት:: በመዓዛ ፍቅርከ ክርስቶስ ሰማዕት ነሥኡ ሕማማተ ወጻድቃን ዔሉ ገዳማተ)::

**ሐዋርያት፦** የወልድ ሐዋርያት የሕግ ምንጮች፣ የወንጌል ወንዞች፣ የወይራ ቅርንጫፎች፣ የወይን ሐረጎችና የአንዱ ግንድ ቅርንጫፎች ናቸው:: (#በግእዝ፦ አንቅዕተ ሕግ ዘወንጌል አፍላግ አዕፁቀ ዘይት ወዘወይን ሐረግ ሠርፀ አሐዱ ጕንድ ሐዋርያቲሁ ለወልድ)::

## 💗ኅዳር 11 ዘሐና💗

**ነገረ ማርያም፦** ሐና ሆይ የቅዱሳን አባቶችሽ ተስፋ በልጅሽ ተፈጸመ:: አክሊልን ተቀዳጅታ የምትመላለስ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት እነሆ:: የዓለም ቤዛ የሆነች ማርያምን የወለዳችኋት ኢያቄምና ሐና ሆይ ለምኑልን:: ከዕለት ሁሉ ሰንበትን አከበረ:: ከሴቶች ሁሉ ደግሞ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ትሆነው ዘንድ ማርያምን ወደደ:: (#በግእዝ፦ ተፈጸመ ሐና በወለትኪ ተስፋ ቅዱሳን አበውኪ:: ነያ ብእሲት ፈራሂተ እግዚአብሔር አክሊለ ተቀጺላ ታንሶሱ:: ሰአሉ ለነ ሐና ወኢያቄም ዘወለድክምዋ ለማርያም ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም:: እምኵሉ ዕለት ሰንበተ አክበረ ወእምኵሎን አንስት ማርያምሀ አፍቀረ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ ለመንፈስ ቅዱስ)::

## 💓ኅዳር 12 ዘሚካኤል💓

**ቅዱስ ሚካኤል፦** የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሊቅ የአብን ቃል የሚሰማ ሆኖ፣ ራሱን ዝቅ ዝቅ አድርጎ በፈጣሪው ፊት በጉልበቶቹ ሰገደ:: (#በግእዝ፦ ሰማዔ ከዊኖ ቃለ አብ አትሒቶ ርእሶ ሰገደ በብረኪሁ ቅድመ ፈጣሪሁ ሚካኤል ሊቅ ሊቀ መላእክት)::

## ❖ኅዳር 16 ዘኪዳነ ምሕረት❖

**ነገረ ማርያም፦** አምኖ የማርያምን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል ሕይወትንም ያገኛል። እመቤቴ ሆይ አደባባይሽ የመረግድ ቅጽሮችሽ የከርከዴን ናቸው። (#በግእዝ፦ ኵሉ ዘአምነ ወጸውዐ ስማ ለማርያም ውእቱ ይድኅን ወይረክብ ሕይወተ። ዐውድኪ ዘመረግድ እግዝእትየ ዘከርከዴን አረፋትኪ)።

## ❤ኅዳር 21 ዘማርያም❤

**ካህናት፦** ከቅድመ ዓለም እስከ ዘለዓለም ምድርን ያለ ካህናትና ያለ ዲያቆናት አልተዋትም። (#በግእዝ፦ ኢኅደጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም እንበለ ካህናት ወዲያቆናት)።

**እግዚአብሔር፦** የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት በካህናት የታጠረች በመንፈስ ቅዱስ የከበረች ናት። ጽዮን ሆይ ንጉሥሽ ለጠላት አይሸነፍም ሀገርንም አይተዋትም። (#በግእዝ፦ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ሕፅርት ወበመንፈስ ቅዱስ ክልልት። ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየኀድጋ ለሀገር)።

**ነገረ ማርያም፦** ሰማይና ምድር ሳይፈጠር የገነት ምድር ሳትፈጠር ማርያም ፈጽማ የተመሰገነች ነበረች። (#በግእዝ፦ ዘእንበለ ይትፈጠር ሰማይ ወምድር ወዘእንበለ ትሣረር ምድረ ገነት ሀለወት ስብሕት ቅድስት ወቡርክት ይእቲ ማርያም)።

## ▶ኅዳር 24 ካህናተ ሰማይ◀

**ካህናተ ሰማይ፦** የልዑልን መንበር ያጥናሉ፤ የፈጣሪን ቃል ይሰማሉ፤ ንዑዳን ክቡራን ካህናት በጽርሐ አርያም ያድራሉ። የካህናተ ሰማይ መልካቸው እንደ መረግድ ነው። ልብሳቸውም እንደ በረዶ ነጭ ነው። (#በግእዝ፦ መንበረ ልዑል የዐጥኑ ቃለ ፈጣሪ ይሰምዑ ብፁዓን ካህናት ጽርሐ አርያም የኀድሩ። ለካህናተ ሰማይ ኅብራቲሆሙ ከመ መረግድ ወአልባሲሆሙ ጸዓዳ ከመ በረድ)።

**ካህናት፦** ካህናትን መረግድ አላቸው። እጆቻቸው እሳትን ይዳስሳሉ። ከሌዊ ልጆች ሥርዓቶችን አሳየ። በምስክሩ ድንኳን ካህናት አድርጎ ሾማቸው። (#በግእዝ፦ ለካህናት ሰመዮሙ መረግደ እደዊሆሙ ይገሣ ነደ። እምደቂቀ ሌዊ አርአየ ሰብዓተ ሥርዓታተ በደብተራ ስምዕ ሤሞሙ ካህናተ)።

**ሥላሴ፦** የዕለት እንጀራችንን ሰጥተውናልና ለሥላሴ ምስጋና ይገባል። (#በግእዝ፦ ለሥላሴ ይደሉ ስብሐት እስመ ወሀቡነ ሲሳየ ዕለት)።

## ➡ኅዳር 25 ዘመርቆሬዎስ⬅

**መርቆሬዎስ፦** የተጋድሎው ነገር ለመናገር የሚጣፍጥ ትርጓሜው መርቆሬዎስ የሆነ ፒሉፓዴር የሚባል አንድ ሰው ነበረ። ባስልዮስና መርቆሬዎስ የቅዱስ መርቆሬዎስ ሥዕል ባለበት ቦታ ጸለዩ። ሥዕሉም እሺ እንደሚል አዘንብሎ ጸሎታቸውን ሰማ። ጠላታቸውንም ገደለ። (#በግእዝ፦

*ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ዘስሙ ፒሉፓዴር ዘበትርጓሜሁ መርቆሬዎስ ብሂል ነገረ ገድሉ መዓርጊር ለተናግሮ። ጸለዩ ባስልዮስ ወጎርጎርዮስ ኀበ ሥዕሉ ለቅዱስ መርቆሬዎስ ደነነ ሥዕል ከመ አሆ ዘይብል ሰምዖሙ ጸሎቶሙ ወቀተለ ፀሮሙ)።*

## 🍒ታኅሣሥ 3 ዘበአታ🍒

**ነገረ ማርያም፦** የወልድን መስቀል ተሸክማችሁ ለማርያም ዘምሩ። እንደ ሲና ታቦት ዘዶር ንጽሕተ ንጹሓን ሆና በቤተ መቅደስ በንጽሕና ኖረች። ምግቧ መና የተባለ ምግብ ነበር። መጠጧም የጽሙና መጠጥ ነበር። *(#በግእዝ፦ ለማርያም ዘምሩ መስቀሎ ለወልድ እንዘ ትጸውሩ። ንጽሕተ ንጹሓን ከዊና ከመ ታቦተ ዶር ዘሲና ውስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በቅድስና ሲሳያ ኅብስተ መና ወስቴሃ ስቴ ጽሙና)።*

## ❖ዘብርሃን❖

**ሥላሴ፦** አብ ጎሕ ነው። ወልድ ጎሕ ነው። በብርሃኑ ጸዳል ጨለማ የተወገደበት መንፈስ ቅዱስም ጎሕ ነው። አቤቱ የምክርህ አበጋዝ፣ የሚቤዥ፣ የሚያድን በሆነና በኋላ ዘመን በላክልን በተወዳጅ ልጅህ እናመሰግንሃለን። *(#በግእዝ፦ አብ ጎሕ ወልድ ጎሕ ወመንፈስ ቅዱስ ጎሕ ዘበጸዳለ ብርሃኑ ሰሰለ ጽልመት። ነአኲተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈኖከ ለነ ወልደከ መድኅነ ወመቤዝወ መልአከ ምክርከ)።*

## 🍎ታኅሣሥ 22 ዘደቅስዮስ🍎

**ደቅስዮስ፦** የሁሉ ጌታ የሆነ የደቅስዮስ ዙፋኑ የእሳት ጣራው የውሃ ነው። *(#በግእዝ፦ እሳት መንበሩ ማይ ጠፈሩ ለደቅስዮስ ለእግዚአ ኵሉ)።*

## ●ታኅሣሥ 30●

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሕፃናትን በማሕፀን የሚሥል እርሱ ራሱ ተሳለ። ከድንግል ተወለደ። *(#በግእዝ፦ ሠዓሌ ሕፃናት ተሥዕለ በውስተ ማሕፀን እምድንግል ተወልደ)።*

## 🍏ጥር 11 ዘጥምቀት🍏

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሰው ሆኖ ታየ። በየጥቂቱ አደገ። በሠላሳ ዓመት በዮርዳኖስ ተጠመቀ። መንፈስ ቅዱስ ውሆችን ይቀድስ ዘንድ ወረደ። ያ ቃል ሥጋ ሆነ። የማይነካ የማይዳሰስ መንፈስ ሲሆን በሥጋ ተዳሰሰ። *(#በግእዝ፦ አስተርአየ ከመ ሰብእ በበሕቅ ልህቀ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ። ወረደ መንፈስ ቅዱስ ከመ ይቀድስ ማያተ። ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወተገሠ በሥጋ መንፈስ ዘኢይትገሠሥ ወዘኢይትለከፍ)።*

## ✿ጥር 12 ዘቃና✿

**ሥላሴ፦** በትጉሃን ዘንድ የሚመሰገን በአንድነት የሚሠለስ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። በዐይን የማይረዱት ረቂቅ መንፈስ የማይዳሰስ የሕይወት እሳት ነው። ለሦስቱ አንዲት ስግደትን

እንሰግዳለን። (#በግእዝ፦ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበተዋሕዶ ይሤለስ እምኀበ ትጉሃን ይትቄደስ። እሳተ ሕይወት ዘኢይትገሠሥ ወዘኢይጤየቅ ለዐይን ረቂቅ መንፈስ። ንስግድ ለሠለስቱ አሐተ ስግደተ)።

### ❃ጥር 13 ዘእግዚአብሔር አብ❃

**ነገረ ክርስቶስ፦** ደም ግባቱ ድንቅ ነው። ከሰው ይልቅ ያምራል። ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅና የዋህ ነው። (#በግእዝ፦ መንክር ላሕዩ ይሤኒ እምሰብእ። ጻድቅ ወየዋህ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ)።

### ❃ጥር 18 ዘጊዮርጊስ❃

**ቅዱስ ጊዮርጊስ፦** የሆድ ዕቃው እስኪታይ ድረስ ቀደዱ። ሥጋውን ቆረጡ። ዐፅሙን ወደ ጉድጓድ ጣሉ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ጠላቶቹን አሸነፈ። (#በግእዝ፦ ንዋየ ውስጡ እስከ ይትረአይ ሰተሩ ሥጋሁ መተሩ ውስተ አዘቅት ዐፅሞ ወገሩ። ቅዱስ ጊዮርጊስ ሞዖሙ ለፀሩ)።

### ❃ጥር 19 ዘገብርኤል❃

**ነገረ ክርስቶስ፦** ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወታችን ምልክት [ትምህርት] ነው። (#በግእዝ፦ ትእምርተ [ትምህርተ] ሕይወትነ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ)።

### ✿ጥር 21 ዘማርያም✿

**ነገረ ማርያም፦** ሞት ለሚች ይገባል። የማርያም ሞት ግን ለሁሉ ይደንቃል። ስለዚህ ወልድ በፍርድ እንደማያዳላ ዕወቁ። እናቱ ሞትን ትቀምስ ዘንድ በርቱዕ ቃሉ አዘዘ። አደባባዮቿ የእውነት ሜዳዋ የዕንቍ፣ የማዳን ደጅ፣ አዲስ ግንብ ናት። ማርያም ግን የበኵር ልጅ የነፍሳችን ጠባቂ ቤዛችንን ወልድን ወለደች። (#በግእዝ፦ ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለማርያም የዐፅብ ለኵሉ እንበይነዝ አእምሩ በውስተ ፍትሕ ከመ ኢያደሉ ትጥዐም ሞተ እሙ አዘዘ ወልድ በርቱዕ ቃሉ። ዐውዳኒ ዘጽድቅ ወመርሕባኒ ዘዕንቍ አንቀጸ አድኅኖ ሐዳስ ንድቅ። ማርያምሰ ወለደት ወልደ ዘበኵሩ ቤዛነ ዐቃቤ ነፍሳቲነ)።

### ❁ጥር 27 ዘመድኀኔዓለም❁

**ነገረ ክርስቶስ፦** የሚበላ እሳት ሆኖ ሳለ መለኮቱን በሥጋችን ሠወረ። (በግእዝ፦ እንዘ እሳት በላዒ ውእቱ ውስተ ሥጋነ ኀብአ መለኮቶ)።

### ❧የካቲት 8 ዘልደተ ስምዖን❧

**ስምዖን፦** የእሳት ነበልባል በሽማግሌ እቅፍ ተያዘ። [ሽማግሌውም] ኪሩቤልን መሰለ። (#በግእዝ፦ ነበልባለ እሳት ተፀውረ ዲበ ሕፅነ ብሉይ ወተመሰለ ከመ ኪሩቤል)።

## የካቲት 15 ዘቂርቆስ

**ቂርቆስ ወኢየሉጣ፦** በሰማያት ደስተኞች የሆኑ ቂርቆስና እናቱ በጽናትና በትዕግሥት በኀይልና በሥልጣን ሰይጣንን አሸነፉት፡፡ (#በግእዝ፦ በጽንዕ ወበትዕግሥት በኀይል ወበሥልጣን ሞዕዎ ለሰይጣን ቂርቆስ ወእሙ በሰማያት ፍሡሓን)፡፡

## የካቲት 16 ዘኪዳነ ምሕረት

**ነገረ ማርያም፦** ድንግል ሆይ ወልድ በጽዮን ተራራ በነገሠ ጊዜ ከቡሩካን በጎች ጋር እንቆም ዘንድ አድዩን፡፡ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የወይን ቦታ የሆነች የቅድስት ድንግልን መታሰቢያዋን ልናደርግና ልናመሰግናት ይገባል፡፡ (#በግእዝ፦ አመ ይነግሥ ወልድ በደብረ ጽዮን ክፍልኒ ድንግል እቁም በየማን ምስለ አባግዕ ቡሩካን፡፡ መፍትው እንከ ንወድሳ ወንግባር ተዝካራ ለቅድስት ድንግል አፀደ ወይን መሶበ ወርቅ እንተ መና)፡፡

## የካቲት 27 ዘመድኀኔዓለም

**ነገረ ክርስቶስ፦** ስምህ የሚጣፍጥና ወንበዴውን የጠራህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በሰማያት ባለ ሰርግህ ጥራን፡፡ የአርያም በግ ሆይ በጽዮን ተራራ ጫፍ የቆምክ ነህ፡፡ (#በግእዝ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ወጸዋዕኮ ለፈያታይ ጸውዐነ ውስተ ከብካብከ ዘበሰማያት፡፡ ኦ በግዕ ዘአርያም በርእሰ ደብረ ጽዮን ዘቆምከ)፡፡

## መጋቢት 10 ዘመስቀል

**መስቀል፦** ስለዚህም የቅዱስ ወንጌል መምህራን እንደ ልዑል ፈጣሪ ለድንግል ማርያምና ለመስቀል እንድንሰግድ አዘዙን፡፡ (#በግእዝ፦ ወበእንተዝ አዘዙነ መምህራነ ቅዱስ ወንጌል አምሳለ ፈጣሪ ልዑል ንስግድ ለመስቀል ወለማርያም ድንግል)፡፡

**ነገረ ክርስቶስ፦** በክቡር ደምህ ትቀድሳት ዘንድ [አቤቱ] ስለቤተክርስቲያን በአደባባይ ፊትህን ተመታህ፡፡ (#በግእዝ፦ ዘበእንቲኣሃ ለቤተክርስቲያን ተጸፋዕከ በውስተ ዐውድ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር)፡፡

## ዘሆሣዕና

**ነገረ ክርስቶስ፦** ደናግልን እንዳያለቅሱ የከለከለ የመስቀል ቀንበርን ተሸክሞ እስከ ቀራንዮ ድረስ ሄደ፡፡ (#በግእዝ፦ ኢይብክያ ዘከልዐ ደናግለ አርዑተ መስቀል ፆረ እስከ ቀራንዮስ ሖረ)፡፡

## ሚያዝያ 10 ዘመስቀል

**ነገረ ክርስቶስ፦** ልጅሽ በበቀል መኀናጸፊያ አጊጦ ሲመጣ ያን ጊዜ የወጉት ያለቅሳሉ፡፡ ቤተክርስቲያን የኢየሩሳሌም ልጆች ሆይ ወደ ንጉሣችሁ ውጡ ትላለች፡፡ አክሊልን አቀዳጁት በእንጨት ላይ ሰቀሉት፡፡ (#በግእዝ፦ አመ ይመጽእ ወልድኪ ሞጣሕተ በቀል ተሠርጊዎ አሜሃ

ይበክዩ እለ ወግዕዎ:: ትብል ቤተክርስቲያን አዋልደ ኢየሩሳሌም ፃኣ ትርአያ ኀበ ንጉሥክን አክሊለ አስተቀጸልዎ ዲበ ዕፅ ሰቀልዎ)::

## ሚያዝያ 23 ዘጊዮርጊስ

**ቅዱስ ጊዮርጊስ፦** ሰማዕት ጊዮርጊስ ሆይ ስምህ እንደ ጊደር ወተትና እንደ ገነት ወይን ይጣፍጣል:: (#በግእዝ፦ ከመ ሐሊብ ዘዕጎልት ወከመ ወይን ዘገነት ይጥዕም ስምከ ጊዮርጊስ ሰማዕት)::

## ግንቦት 1 ዘማርያም

**ነገረ ማርያም፦** ለብዙዎች ቤዛ ለመሆን አንቺን መልካሟን የፈጠረ እግዚአብሔር ይባረክ ስሙም ይመስገን:: አንቺ ለዓለም ሕይወት ሁሉ መሠረት ነሽና:: ሁለት አሮጊቶች ልቅሶን ባለቀሱ ጊዜ በደልን ይቅር የምታስብልና ለሁላችን ለወንጌላውያን መሸሻ የሆነችን ሴት ልጅን አገኙ:: ኢያቄምና ሐና ሰማይን ወለዱ ሰማያቸውም ፀሐይን አወጣች:: ዳግሚት ሰማይ ዛሬ ተወለደች:: ድንግል ሆይ በሕግ በሆነ ግንኙነት ከኢያቄምና ከሐና ተወለድሽ እንጂ በፍትወት የተፀነስሽ አይደለሽም:: ነጭ ርግብ፣ መሠረቷ የዕንቍ፣ ቤቷ የጳዝዮን የሆነች [ማርያም] ዛሬ በይሁዳ ምድር ተወለደች:: ነቢያትንና ጻድቃንን ትቤዥ ዘንድ ማርያም ከሐናና ከኢያቄም በመወለዷ ዛሬ ደስታ ሆነ:: (#በግእዝ፦ ይትባረክ እግዚአብሔር ወይትአኰት ስሙ ኪያኪ ሠናይተ ዘፈጠረ ለቤዛ ብዙኃን እስመ መሠረት አንቲ ለሕይወተ ኵሉ ዓለም:: ክልኤቱ አዕሩግ አመ በከዩ ብካየ ረከቡ ወለተ ዘታስተሠሪ ጌጋየ ለወንጌላውያን ኵልነ ዘኮነተነ ምጕያየ ኢያቄም ወሐና ወለዱ ሰማየ ሰማዮሙኒ አሥረቀት ፀሐየ:: ተወልደት ዮም ዳግሚት ሰማይ:: ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተፀነስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ:: ርግብ ጸዓዳ ዘዕንቍ ድዳ ወዘጳዝዮን ማኅፈዳ ተወልደት ዮም በምድረ ይሁዳ:: ዮም ፍሥሓ ኮነ በእንተ ልደታ ለማርያም እምሐና ወኢያቄም ከመ ትቤዙ ነቢያተ ወጻድቃነ)::

## ግንቦት 4 ዘዮሐንስ

**ነገረ ክርስቶስ፦** የሕይወት ነገርን እየተናገራቸው ጎኑን በጦር ጫፍ ወጉት (#በግእዝ፦ ረገዝዎ ገቦሁ በአፈ ኵናት እንዘ ይትናገሮሙ ነገረ ሕይወት)::

## ግንቦት 11 ዘያሬድ

**ቅዱስ ያሬድ፦** የትንሣኤውን ክብር የሚናገር የእግዚአብሔር አገልጋይ የማሕሌታይ ያሬድ ኦሪት ማዘቢያው ወንጌል ጫማው ነው:: (#በግእዝ፦ ያሬድ ማሕሌታይ ለእግዚአብሔር ካህኑ ስብሐተ ትንሣኤሁ ዘይዜኑ ኦሪት ቶታኑ ወወንጌል አሣዕኑ)::

## ዘዕርገት

**ነገረ ማርያም፦** ከምድር እስከ ሰማይ መውጫ የሆንሽን ሆይ የፍጥረት መጀመሪያ የሆነ [አዳም] በአንቺ ታደሰ። (#በግእዝ፦ ኦ ምዕራግ እምድር እስከ ሰማይ ወብኪ ተሐደሰ ቀዳሜ ኵሉ ፍጥረት)።

## ግንቦት 24 ዘተክለ ሃይማኖት

**እግዚአብሔር፦** እናመልከው ዘንድ እኛን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። (#በግእዝ፦ ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ)።

## ሰኔ 12

**እግዚአብሔር፦** የሚመክረው አይፈልግም የሚረዳውም አይፈልግም። ኀይሉን ማሸነፍ የሚችል የለም። (#በግእዝ፦ ኢይጽሕቅ ዘይመክሮ ወኢየኀሥሥ ዘይረድኦ አልቦ ዘይክል መዊዐ ኀይሉ)።

## ሐምሌ 5

**ጴጥሮስ ወጳውሎስ፦** ጴጥሮስ ጳውሎስን ወንድሜ ጳውሎስ ሆይ ጨክን አትጠራጠርም ከዚህ በኋላ አንሞትም አለው። (#በግእዝ፦ ይቤሎ ጴጥሮስ ለጳውሎስ ጥባዕኬ እኁየ ጳውሎስ ወኢትናፍ*ቅ እምዝ ዳግመ ኢንመውት)።

## ሐምሌ 7 ዘሥላሴ

**ቅድስት ሥላሴ፦** ሥላሴ ትደነቃለች እንጂ አትነገርም። በሥላሴ በሰማይና በምድር ትኖራለህ። (#በግእዝ፦ ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር እስመ በሥላሴ ትሄሉ በሰማይ ወበምድር)።

## ነሐሴ 24 ዘተክለ ሃይማኖት

**ምጽአት፦** ያንጊዜ በቀኙ ያሉትን የአባቴ ቡሩካን ወደእኔ ኑ ይላቸዋል። ማርና ወተትን የምታፈስ አዲስ ምድርንም ያወርሳቸዋል (#በግእዝ፦ አሜሃ ይብሎሙ ለእለ በየማኑ ንዑ ለአቡየ ቡሩካኑ ወያወርሶሙ ምድረ ሐዳሰ እንተ ታውሕዝ ሐሊበ ወመዓረ)።

## መዝሙር

**ነገረ ክርስቶስ፦** የሰላም ንጉሥ ክርስቶስ ሆይ ልዕልናህ ታላቅ ነው ክብርህም ድንቅ ነው። በቆላ እንዳለ የሱፍ አበባ የቅዱሳን መዓዛቸው ነህ። የበረከት ፍሬ የገነት ሐመልማል ነህ። ለቅድስት ቤተክርስቲያንም መሠረቷና ምሰሶዋ ነህ። ከሰው ሰው ይሆን ዘንድ ያለው [ወልደ እግዚአብሔር] በወገቡ የተሠወረበት ያዕቆብ እስኪመጣ ድረስ ብዙ እረኞች ከጉድጓዱ አፍ ድንጋዩዋን ማንሣት አልቻሉም። [አቤቱ] ቃልህ ሰላም ፍርድህ እውነት ነው። እኛን ይቤዥ ዘንድ ጌታ ባሪያ ሆነ። አስቀድሞ ብዙ ሙታንን አስነሥቶ በሦስተኛው ቀን ተነሣ። በእኛ ፍቅር የተነሣ እስከ ሞት ደረሰ። ክርስቶስን በእምነት ቃል ያመሰግኑት ዘንድ ዛሬ ሰውና መላእክት አንድ መንጋ ሆኑ።

ዛሬ በየነገዳቸው የወልድን ፋሲካ ያከብራሉ:: እርሱ ለዘሪ ዘርን ይሰጣል:: እህልን ለምግብ ያሳምራል:: የተቸገረን ከምድር ያስነሣል:: መመገብን የምትችል [አቤቱ] መግበን:: (#በግእዝ፦ ንጉሠ ሰላም ክርስቶስ ዐቢይ ልዕልናከ ወመንክር ስብሐቲከ:: መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ከመ ጽጌ ደንጎላት ዘውስተ ቈላት:: ሐመልማለ ገነት አስካለ በረከት:: ዐምዳ ወድዳ ለቅድስት ቤተክርስቲያን:: ወብዙኃን ኖሎት መጽኡ ወስዕኑ ከሢቶታ ለዕብን እምአፈ አዘቅት እስከ ይመጽእ ያዕቆብ ዘክቡት ውስተ ሐቋሁ ዘሀሎ ይሠነ እምሰብእ:: ወከማሁ መጽኡ ብዙኃን ነቢያት ወስዕኑ ከሢቶታ ለጥምቀት እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ እምሰማይ:: ሰላም ቃልከ ወጽድቅ ኵነኔከ:: ከመ ኪያነ ይቤዙ እግዚእ ኮነ ገብረ:: ብዙኃነ ሙታነ አንሥኦ ቅድመ ውእቱ ተንሥአ በሣልስት ዕለት:: በፍቅረ ዚኣነ በጽሐ እስከ ለሞት:: ዮም አሐደ መርዔተ ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን:: ዮም ይገብሩ በዓለ በበነገዶሙ ፋሲካሁ ለወልድ:: ውእቱ ይሁብ ዘርዐ ለዘራዒ ያሠምር እክለ ለሲሳይ ያነሥኦ እምድር ለነዳይ:: ዘትክል ሴስዮ ሴስየነ)::

**መልካም ምግባር፦** ሰው ሆይ የሞትህን ቀን አስብ:: ነፍስህ የምትወጣበትን ጊዜም አስብ:: ተረዳ ዕወቅ አስተውልም:: የሰው ሀብቱ እንደ ዱር አበባ ነው:: የዱር አበባም በጊዜው ያልፋል ሁሉ በጊዜው ያልፋል:: የማያልፍ የለም:: ከላያችን ላይ የጨለማ ሥራን ጥለን የጽድቅ ጋሻን እንልበስ:: ኃጢአት በሚሠረይበት ገንዘብ ጾምን ለንስሓ ሰጠን:: ራሳችንን ለጽድቅ እናስገዛ በተንኮል አንመላለስ:: ሕይወታችን በወንጌል ሆነ:: እናት ልጇን በማታድንበት ቀን፣ ምድርም አደራዋን በምትመልስ ጊዜ፣ አብ የፍዳ ልብስን በለበሰ ጊዜ፣ በሚያስፈራ አደባባይ በሚወቅሰን ጊዜ፣ በፍዳ ጊዜ፣ በፍርድ ቀን፣ በእግዚአብሔር ቀን ነፍስን ምን እንላታለን? ያን ጊዜ ሥራችን ተገልጦ ይሰጣል:: የሠራነው ሁሉ ይነበባል:: ፀሐይ ወጣ፣ መለከት ተነፋ፣ አዋጅ ነጋሪ ደረሰ፣ ዘፋን ለፍርድ ቀና፣ የደከሙ ይደሰታሉ፣ የሰነፉ ይደነግጣሉ:: በሕይወታቸው የተገዙለትን ፊቱን ባዩ ጊዜ በቀኙ ያሉት ይደሰታሉ:: እንደ ቸር አገልጋይ ለእግዚአብሔር ተገዙ:: (#በግእዝ፦ ኦ ሰብእ ዕለተ ሞትከ ተዘከር ወጊዜ ፀአታ ለነፍስከ ዑቅ ወጠይቅ አእምር ወለቡ:: ብዕሉሰ ለሰብእ ከመ ጽጌ ገዳም:: ጽጌ ገዳምኒ በጊዜሁ የኀልፍ ኵሉ በጊዜሁ የኀልፍ:: ወዘኢየኀልፍ አልቦ:: ንግድፍ እምላዕሌነ ኵሎ ምግባረ ጽልመት ወንልበስ ወልታ ጽድቅ:: ወሀበነ ጾመ ለንስሓ በዘይሠረይ ኃጢአት:: ናግርር ርእሰነ ለጽድቅ ኢንሑር በትምይንት:: በወንጌል ኮነ ሕይወትነ:: አመ ዕለተ ፍዳ አመ ዕለተ ደይን አመ ዕለተ እግዚአብሔር ምንተ ንብላ ለነፍስ አመ ኢታድኅን እም ውሉዳ ወምድርኒ አመ ታገብዕ ማኅፀንታ አመ ይለብስ አብ ልብሰ ፍዳ አመ ይወቅሰነ በግርምት ዐውድ:: አሜሃ ይትከሠት ወይሰጣህ ምግባራቲነ ወይትነበብ ኵሉ ዘገበርነ:: ፀሐይ ሠረቀ ቀርን ጸርሐ ዐዋዲ በጽሐ መንበር ረትዐ ለኰንኖ እለ ፃመዉ ይትፌሥሑ ወእለ ተሐከዩ ይደነግፁ:: እለ በየማኑ ይትፌሥሑ ሶበ ይሬእዩ ገጾ ለዘሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ:: ከመ ገብር ኄር ለእግዚአብሔር ተቀነዩ)::

**ትርጓሜ፦** አዝመራው የዓለም መጨረሻ ነው አጫጆችም መላእክት ናቸው:: (#በግእዝ፦ ማዕረሩሰ ኅልቀተ ዓለም ውእቱ ወአፀዱኒ እሙንቱ መላእክት)::

**ነገረ ማርያም፦** ማርያም ግን እናቱም ናት አገልጋዩም ናት:: ድንግልም ናት ሰማይም ናት:: የመለኮት ማደሪያ አላት:: ከንፈሮቿ እንደ ቀይ አበቦች ቀይ ናቸው:: የአፏ መዓዛ እንደ እንኮይ

ነው። ተስፋ ለቆረጡት ተስፋቸው፣ በእውነት ንጹሕ ዝናም የሆንሽ፣ የክርስቲያን ሰንበት የተባልሽ ማርያም ሆይ ለምኚልን። ድንግል ከፍጥረት ሁሉ ትበልጣለች። የመለኮት እሳት አላቃጠላትም። (#በግእዝ፦ ማርያምሰ እሙኒ አመቱኒ ድንግልኒ ሰማይኒ ይእቲ። ሰመያ ማኅደረ መለኮት። ከመ ፍሕሦ ቀይሕ ከናፍሪሃ መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል። ሰአሊ ለነ ማርያም ሰንበተ ክርስቲያን ተስፋ ቅቡፃን እንተ በአማን ንጹሕ ዝናም። ድንግል ተዐቢ እምኵሉ ፍጥረት ኢያውዐያ እሳተ መለኮት)።

**❀ወርኀ በዓል❀**

**ነገረ ክርስቶስ፦** ሥጋችንን ለብሶ ወደ ዓለም መጥቷልና ዛሬ መላእክት እልል ይላሉ የመላእክት አለቆችም ይዘምራሉ። መድኅን ወደ እኛ መጥቷልና። ንጹሕ በግ ታረደ። አንተን ሁልጊዜ ያዩ ዘንድ አቤቱ የዕውቀት ዓይኖችን ስጠን። (#በግእዝ፦ ዮም መላእክት ይዬብቡ ወሊቃነ መላእክት ይዜምሩ እስመ መጽአ ውስተ ዓለም ለቢሶ ሥጋነ እስመ መድኅን መጽአ ኀቤነ። በግዕ ንጹሕ ተጠብሐ። ሀበነ እግዚኦ አዕይንተ አእምሮ ከመ ኪያከ ወትረ ይርአያ)።

**ነገረ ማርያም፦** የእግዚአብሔር የመቅደሱ ተራራ ማርያም ሆይ ሰላም ለአንቺ ይሁን። (#በግእዝ፦ ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር ማርያም ሰላም)።